መገናኛ፡- Kassie McKnight-Xi
Mcknight-xi.k@portseattle.org

በቀጥታ የሚለቀቅ
ማርች 3፣ 2025

# በSouth King County የማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ (South King County Community Impact Fund) በኩል፣ የ $2 ሚሊዮን የኢኮኖሚ እድሎች አሉ

*የማመልከቻ ግዜ እስከ አፕሪል 10፣ 2025 ድረስ ክፍት ነው*

**SEATTLE –** Seattle ወደብ የSouth King County ማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ (South King County Community Impact Fund, SKCCIF) የማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች (Economic Opportunities for Communities, EOC) ፕሮግራም፣ አሁን በ Seattle-Tacoma International Airport (SEA) እና South King County፣ Duwamish Valley እና Beacon Hill ዙሪያ ባሉ በታሪካዊ ብዙም ባልተወከሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ለማሳደግ ከማህበረሰብ-ተኮር ድርጅቶች ማመልከቻዎችን እየተቀበለ ነው።

በዚህ ዙር በአጠቃላይ $2 ሚልዮን ይገኛል። ድርጅቶች ለአንድ ዓመት እስከ $115,000፣ እንዲሁም ለብዙ ዓመታት (እስከ 3 ዓመታት) ከ$100,000 እስከ $275,000 የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ። የማመልከቻ ግዜ እስከ አፕሪል 10፣ 2025 ድረስ ክፍት ነው። 501(c)3፣ 501(c)6 ወይም የገንዘብ አያያዝ 501(c)3፣ 501(c)6 ድጋፍ ያላቸው ማህበረሰብ ተኮር የሆኑ ድርጅቶች ለማመልከት ብቁ ናቸው።

**የ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች (Economic Opportunities for Communities, EOC) ፕሮግራም አመጣጥ**

ቀደም ብሎ የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም (Economic Recovery Program) የነበረው የማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች (Economic Opportunities for Communities, EOC) ፕሮግራም፣ በ South King County ውስጥ ብዙም ያልተወከሉ ማህበረሰቦችን ለመኖር የምያስችል ደሞዝ ያላቸው ስራዎች እና ከወደብ ጋር በተያያዙ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የስራ እድሎችን ያገናኛል። የገንዘብ ድጋፉ፣ ለቀጣዩ ትውልድ ባለሙያዎች በአቪዬሽን፣ በግንባታ ንግድ፣ በአረንጓዴ ስራዎች እና በባህር መስክ እንቅስቃሴዎች ወደ ስራ እንዲገቡ ግንዛቤ እና ተደራሽነትን የሚፈጥሩ ማህበረሰብ-መር የሙያ ዝግጅት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶችን ይደግፋል።

"ይህ እድል፣ የአካባቢ እና ኢኮኖሚያዊ አለመመጣጠን ለሚያጋጥሟቸው ማህበረሰቦች የወደብ ገንዘብ ተደራሽነትን ይፈጥራል፤ አብዛኛዎቹ ከዚህ በፊት ከእኛ የገንዘብ ድጋፍ አግኝተው አያውቁም፣“ **ሲሉ የSeattle ወደብ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት (Seattle Port Commission President) Toshiko Hasegawa ተናግረዋል።** ”ለጉዳዩ ቅርብ በሆኑ ማህበረሰቦች የ $14 ሚሊዮን ቀጥተኛ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ከዚህ ቀደም ያልታየ ሲሆን፣ መፍትሔዎች ላይ እሰራ ነው።"

በ 2020፣ ማህበረሰቦች ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ አስከፊ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ እንዲያገግሙ ለመርዳት የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም (Economic Recovery Program) ተቋቋመ። በ 2025፣ በማህበረሰብ የማዳመጥ ክፍለ

መገናኛ፦ Kassie McKnight-Xi
Mcknight-xi.k@portseattle.org

ጊዜዎች፣ የአጋር ግብረመልስ እና የፍትሃዊነት ጠቋሚን (Equity Index) በመጠቀም፣ ከማገገም ይልቅ ኢኮኖሚያዊ እድልን ለማራመድ የገንዘብ ድጋፍ ላይ እንደገና በማተኮር፣ የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም (Economic Recovery Program) ወደ EOC ፕሮግራም ተቀየረ።

“ይህ የ $2 ሚሊዮን ፕሮግራም ጥሩ ክፍያ ወደሚያስገኝ ቤተሰብ የሚደግፉ ስራዎችን ለማስፋፋት ያለንን ቁርጠኝነት ይወክላል፣" ሲሉ የ Port Seattle Commissioner፣ Hamdi Mohamed ተናግሯል። "ፕሮግራማችን በታሪክ ብዙም ባልተወከሉ ተጨማሪ የ South King County፣ the Duwamish Valley እና Beacon Hill አከባቢዎች በማካተት፣ እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደ አቪዬሽን፣ የባህር እንቅስቃሴ፣ ግንባታ እና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ያሉ በማደግ ላይ ባሉ ዘርፎች የስልጠና እና የሙያ ዝግጅት እንዲያገኙ እያረጋገጥን ነው። ከ የአጭር ጊዜ ማገገሚያ ወደ የረጅም ጊዜ እድል እየተሸጋገርን ነው - በአካታች የሰው ሃይል ላይ የተገነባ የበለጠ ጠንካራ ክልል መፍጠር።"

በ2025-2029 ውስጥ የገንዘብ ድጋፍ ዙሮች ሌሎች የሚከተሉትን ለውጦች ያካትታሉ፦

- የ Seattle ፍትሃዊነት መረጃ ጠቋሚ (Seattle’s Equity Index) ያለመመጣጠን አለ ብሎ የለያቸውን የ South King County፣ Duwamish Valley እና Beacon Hill አካባቢዎችን ለማካተት የጂኦግራፊያዊ ክልሉን ማስፋፋት
- በአውሮፕላን ማረፊያ አቅራቢያ ለሚገኙት ስድስት ከተሞች የወደቡ ቁርጠኝነት ቅድሚያ መስጠት እና በእነዚያ ከተሞች ውስጥ የፕሮጀክቶች ማመልከቻዎች የቅድሚያ ደረጃን እንዴት እንደሚያገኙ መለየት

**ወደብ-ነክ ኢንዱስትሪዎች ግንኙነቶች**
ከሁሉም የ Washington ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር እና ከ500 በላይ በተቋሙ ውስጥ ከሚሰሩ አሰሪዎች ጋር በመገናኘት፣ በወደቡ ስራዎች በጣም የተጎዱ ማህበረሰቦችን የሚጠቅሙ ጥሩ ደሞዝ የምያስገኙ ስራዎችን በመስራት ወደቡ በልዩ ሁኔታ ተቀምጧል። ብዙ ከወደብ ጋር ግንኙነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች የሰው ኃይል እጥረት እያጋጠማቸው በመሆኑ፣ የሰው ኃይል ልማት ኢንቨስትመንቶች ወሳኝ ናቸው። ማህበረሰብ መር የሙያ-ዝግጅት ፕሮግራሞች፣ ተሳታፊዎች በእነዚህ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ እና ቤተሰብ ለማስተዳደር የሚበቃ ደሞዝ ያላቸው ስራዎችን ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉትን ተጋላጭነት፣ ችሎታ፣ ልምድ እና ስልጠና እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

"ConstructDiversity የግንባታ ኢንዱስትሪውን ገጽታ በመቀየር ረገድ ከፍተኛ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። ፕሮግራማችን በሮችን ብቻ አደለም እየከፈተ ያለው፤ በSouth King County ውስጥ ብዙም ባልተወከሉ ወጣቶች ዘላቂ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ድልድይ እየገነባ ነው፣" **ሲሉ የ ConstructDiversity ምክትል ሓላፊ እና የቦርድ አባል Rodell Razor ተናገሩ**። ፍትሃዊ ተደራሽነትን፣ ማማከርን እና የተግባር ልምድን በማቅረብ፣ በግንባታ እና ተዛማጅ መስኮች ውስጥ ያለውን ልዩነት በመጨመር ተጨባጭ ውጤቶችን እያየን ነው። ተፅዕኖው ከግለሰብ የስኬት ታሪኮች ባሻገር ይዘልቃል - ኩባንያዎችን፣ ማህበረሰቦችን እና ሰፊውን ኢኮኖሚ የሚጠቅም የበለጠ አሳታፊ የሆነ የኢንዱስትሪ ባህል እያሳደግን ነው። እያደግን ስንሄድ፣ ኑሮ እየቀየርን ብቻ ኣደለም፤ የግንባታውን የወደፊት ሁኔታ እያስተካከልን ነው።

Port of Seattle

መገናኛ፦ Kassie McKnight-Xi
Mcknight-xi.k@portseattle.org

**2025 የማመልከቻ ሂደቶች**

ከወደብ ጋር ግንኙነት ባላቸው ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከሠራተኛ ልማት እና የሙያ ዝግጅት ጋር የሚዛመዱ ውጤቶች ያለው ፕሮጀክት አለዎት? ድርጅትዎ፣ በታሪክ ብዙም ባልተወከሉ ማህበረሰቦች ጋር አብሮ የመስራት ልምድ እና እምነት አለው?

የ EOC ድህረገጽ ይጎብኙ፣ ለ፦

- ድርጅትዎ እና የፕሮጀክት ፕሮፖዛልዎ፣ ከዚህ የገንዘብ ድጋፍ መስፈርት ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማወቅ የ SKCCIF EOC ራስ ግምገማ ይውሰዱ።
- ስለ የማመልከቻ ሂደት፣ የፕሮፖዛል ቁሳቁሶች እና ቀደም ሲል ስለተሸለሙ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ይወቁ
- **ለማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ እድሎች የገንዘብ ድጋፍ (Economic Opportunities for Communities Funding) ያመልኩ።**

- ዝመናዎችን በኢመይል ለማግኘትይመዝገቡ

**ስለ South King County የማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ (South King County Community Impact Fund, SKCCIF)**

ወደቡ በፍትሃዊነት ላይ የተመሰረቱ ሽርክናዎችን ለማዳበር እና በታሪካዊ ሁኔታ፣ በዘር፣ በባህል እና ለተለያዩ ለተጎዱ በአየር ማረፊያ አቅራቢያ ለሚገኙ ማህበረሰቦች ሀብትን እና ድጋፍን ለማቅረብ በ 2019 SKCCIFን አቋቋመ። ከ 2020 እስከ 2024፣ SKCCIF አራት ዙር የኢኮኖሚ ማገገም Economic Recovery (የአሁኑ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች (Economic Opportunities for Communities, EOC) እና የአካባቢ እርዳታዎች (Environmental Grants) (የአሁኑ የአከባቢ ማሻሻል (Environmental Improvement)) ፕሮግራሞች አስጀምሯል፤ እነዚህ ፕሮግራሞች የስራ ስልጠና፣ ጥሩ ክፍያ የሚያስገኙ የስራ እድሎችን እና የአካባቢ ማሻሽያዎችን የሚሰጡ ማህበረሰብ-መር ፕሮጀክቶችን ይደግፋሉ። የገንዘብ ድጋፍ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ከ 50 በላይ ድርጅቶች ከ 80 በላይ ለሆኑ ፕሮጀክቶችን በድምሩ $9.25 ሚሊዮን የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

በ 2024፣ የ Seattle ወደብ ኮሚሽን ፍትሃዊነትን፣ የአካባቢ ማሻሻያዎችን እና ከወደብ ጋር በተያያዙ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ስራዎችን እና የስራ እድልን የሚያራምዱ በ SKCCIF ማህበረሰብ ተኮር ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል $14 ሚሊዮን እንደገና ፈቅዷል። SKCCIF፣ ወደቡ ከማህበረሰቡ አባላቶች እና እነዛ ማህበረሰቦችን በማገልገል ከሚገኙ ድርጅቶችን ያለውን ግንኙነት አጠናክሯል።

###

**ስለ Seattle ወደብ**

መገናኛ፡- Kassie McKnight-Xi
Mcknight-xi.k@portseattle.org

*በ1911 በህዝብ ድምፅ እንደ ልዩ ዓላማ መንግስት የተመሰረተው የSeattle ወደብ ተልዕኮው፣ ንግድን፣ ጉዞን፣ ግብይትን እና የስራ ፈጠራን በፍትሃዊነት፣ ተጠያቂነት እና ለአካባቢ በሚስማማ መንገድ በማሳደግ በክልሉ ውስጥ የኢኮኖሚ እድሎችን እና የህይወት ጥራትን ማሳደግ ነው።*

*ወደቡ የ Seattle-Tacoma International Airport (SEA)፣ የNorth Pacific የአሳ አጥማጅ መርከብ መኖርያ የሆነውን የFishermen Terminal እንዲሁም የህዝብ የሆኑ የትንሽ ወደብ መዝናኛ ጀልባዎች ባለቤት እና አስተዳዳሪ ነው። ወደቡ ከሰሜን ምዕራብ የባህር ወደብ ጥምረት (Northwest Seaport Alliance) ጋር በመተባበር፣ ሁለት የመርከብ ሽርሽር መዳረሻዎች፣ የእህል መዳረሻ፣ የሪል እስቴት ንብረቶች እንዲሁም የባህር ሓይል መዳረሻዎች ባለቤት ነው።*

*የወደብ ስራዎች፣ በክልሉ ወደ 200,000 የሚጠጉ ስራዎችን እና $7 ቢሊዮን ደሞዝ ድጋፍ ያግዛሉ። በሚቀጥሉ 13 ዓመታት፣ የወደብ ክፍለ ዘመን አጀንዳ (Port Century Agenda) የሀገሪቱ መሪ አረንጓዴ እና ሓይል ቆጣቢ ወደብ በመሆን በኢኮኖሚ እድገት ተጨማሪ 100,000 ስራዎችን መፍጠር ይፈልጋል። በወደቡ ድህረ ገጽ ላይ ተጨማሪ ይወቁ።*

---